ለክቡር ፕሮፌሰር አፈወርቅ ገ/የሱስ

መቃብር ዓለም

“ምኒሊክ ያሏት መጽሓፍዎን ካነበብኳት ውሎ አድሯል። አባባልዎ፣ አጻጻፈዎ፣ በጠቅላላው ሀሳብዎ ስላስኮረፈኝ ደግሜ መጽሐፈዎን ማየት ቀርቶ ጭራሽ ለማየት ትዝ እንዲለኝ አልፈልግም ነበር። የሚታይ ነገር ስላገኘሁበት እንደገና እንዳያት ተገደድሁ። ይህንንም ደብዳቤ ልጽፍልዎት አሰብኩ። ጻፍኩትም። መጽሐፉ እንደምንም ለማንም ይጻፍ ! ማክያቬሌ ለንጉሣውያን ቤተሰብ እጅ መንሻ መጽሐፍ ጻፈ። ጊዜያዊ ፍላጐቱ ባይሳካለትም እስከ ጊዜያችን ድረስ ብዙ ተከታዮችን አተረፈ። በይፋ ሊያመሰግኑት ባይሹም ሃሳቡን በተግባር በማዋል እንዳይረሳ ያደረጉት መሪዎች ጥቂቶች አይደሉም። ምንም እንኳን ስማቸው ከተግባራቸው መነጻጸሩ ነገሩን ጉልህና ግልጽ የሚያደርገው ቢሆንም አደገኝነቱን ለመረዳት በዚህ ክፈለ ዘመን ባሁኑ ጊዚያት የማክያቪሌ ደቀ መዝሙሮች መኖራቸውን ብቻ ገልጬ ማለፍ በቂ ነው።

“ድንገት ብትገናኙ ይህንኑ ይግለጹለት። አፈወርቅም መጽሐፍዎን እንደጻፉት ይጻፉት፣ በዚህ አልወቅስዎትም። ከርስዎ የባሰ በጊዚያችን መች ጠፋና! ይልቅስ የሚነሳለትን ላንሣ!!

“እስከትላንት ድረስ” አሉ አፈወርቅ ዛሬ ከሞላ ጐደል ትላንትናን እንደሚመስል አላወቁም መሰል (በእነ አፄ ቴዎድሮስና በእነ አፄ ዮሐንስ ጊዜ) የኢትዮጵያ ደሃ ለወታደር መጫዎቻ ነበር ። ባርያ በገዛ ራሱ ማዘዝ እንደማይችል የኢትዮጵያ ድሃም በገዛ ራሱ ማዘዝ አይሆንለትም ነበር። የሚያዝበት ቀርፋፋ ጋሻ ያነገበና አንድ ባለኔ ጦር የያዘ ፣ አንድ የመሸበት ደበናንሳ የጀራረገውና ተሰገባው በሥፍራው ተጣልቶ ፀሐይ የሚሞቅ ጐራዴ መሳይ በወገቡ ያገነበጠ ቅማላም ወታደር ነበር። ደሃው ወታደር ግን እሱን ደስ ላይለው የሌላውን ደስታ ሲከላከል ለገዛ ራሱ ሳያልፍለት የድሃውን ንብረት ሲያፈርስ ይኖር ነበር። ይኸው ወታደር እንኳንስ ተስራ ገብቶ ...... ሄዶም ባደረበት አገር ሳይቀር ደሃውን የፈጥኝ አስሮ ነጭ ኑግ ፣ ጥቁር ወተት ውለዱ ሲልና ባለቤቲቱ (ሚስቲቱ) እንደ ገረድ ባልዮው እንደ ሎሌ ፣ እግር አጥበው አልጋ አንጥፈው ትራፊውን በልተው እነሱ ከምድር እሱ ታልጋ ተኝተው ያድር ነበር።

"ከቶም አንዳንድ ጊዜስ መልከ ቀና ሚስት የነበረችው ባላገር በመከራ ላይ መከራ በግፍ ላይ ግፍ በውርደት ላይ ውርደት ታክሎበት ያድር ነበር።

"ከነዚህኞቹ መከረኞች አንዱ መልከ ቀና ሚስት ነበረችው ። አንድ ቀን በቴዎድሮስ ጊዜ አንድ ነፍጠኛ ተመርቶ ገባና ባለቤቲቱ መልከ ቀና ሆና ባያት ጊዜ ነፍጡን ከጉልበቱ ላይ አድርጎ አንተ ይች እህትህ ስንት አመቷ ነው? ቁርጥ አንተን ትመስላለች አለው። ያ ባላገር ምሽቴ ናት ማለቱን ፈራ። ያም እርጉም ነፍጠኛ በጥፊ እያጣፈረ ምሽቱን ይዞበት አደረ ። ከዚህ በኋላ ያ መከረኛ ድሃ አዘነ። ንዴት ያዘውና፣

"ታገር እኖር ብዬ ከብት እነዳ ብዬ

ልጅ አሳድግ ብዬ

ለባሻ ዳርኩለት ምሽቴን እቴ ብዬ" ብሎ አንጐራጐረ።

ለነዚያ ለንጉሦች የበኸር ልጃቸው ወታደር ብቻ ነበር።

"አለ ድሃ ዘውድ ፣ አለ ገበሬ ማድ ጀግና ማስከተል እንዳይቻል.....

አፈወርቅ በትናትናና በዛሬ መካከል ልዩነት አለመኖሩን ፣ ቢኖርም ትንሽ መሆኑን ቢረዱ ምንኛ በተገረሙ! እርግጥ ጦሩና ጐራዴው በጣም ዘመናዊ በሆኑ በግማሽና ሙሉ አውቶማቲክ መሣሪያዎች ተለውጠዋል።

በገዥና በተገዥ መካከል ያለው ዝምድና ግን እንደነበረ ነው!! ፈትም ለገዥ የተፈጠረ ይመስል ነበር፣ ዛሬም ያው ወታደር ሥርዓተ መሃላውን ሲፈጽም እንኳን ንጉሡ ነገሥቱን፣ አገሩን፣ድንጋዩን ፣ ተራራውንና ሸለቆውን ሊጠብቅ እንጂ ሕዝቡን ሊጠብቅ ቃል አልገባም። ቃል ስላልገባም አይጠብቅም። ወታደር እንደላሚቱ እረኛውን እንጂ ጌታውን አሁንም አላወቀም።

ወታደር (ፖሊስ) ዛሬም ያስራል፣ ይፈርዳል፣ ቤት ይበረብራል፣ ይመዘብራል። ያለፈው ዓመት ሰላማዊ ሠልፍና የዘንድሮው በሰው ልጅ ሥራ ብዕሩ ቢያለቅስ መርዝ ተፋ(ብዕሩ) ተብሎ የታሰረው የሐይሉ ገብረ ዮሐንስ ታሪክ ቋሚ ምስክሮች ናቸው ። እየመጡ ያለፉትንና በጊዜያችን ያሉትን የጀርመን ኤስ ኤስ፣ የሩሲይውያን የሚስጥር ፖሊስ(ኬጂቢ)፣ የአሜሪካን (ሲ.አይ ኤ) የእኛን (ጆሮ ጠቢ) ርኩስ ሥራ

ቢያውቁ ምንኛ ባንገሸገሸዎት !! ስንቶቹን እርስዎን እንደመሰለ አደርጓቸው ፣ ስንቶቹን ለገመድ ፣ ስንቶቹን ለጥይት አሳልፈው ሰጧቸው! ቤት ይቁጠራቸው።

ዓለም የማይጐረብጣትን ካፈር ደባልቃ ታስገዛለች። ከሩቅ ሩቅ ምሳሌ ለመስጠት ሮዴሻንና ደቡብ አፍሪካን መጥቀስ ይበቃል። ዓለም ለክፉም ሆነ ለደግ መልኳን ለመለወጥ የሚሞክሩ ልጆቿን በጭካኔ ታስቀጣለች። ዓመት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ያመፁ ልጆቿን አልገድልም ያለውን ካሴስ ክለይን አምስት ዓመት እስራት አስፈርዳበታለች። ቼጉቤራን ለጥይት አሳልፋ ሰጥታዋለች..... በዓለም ደረጃ ያሉትን መጥቀሴ ነው እንጂ ፣ እንደ ኃይሉ ከየመንደሩ የሚታፈሰውንማ ማን አውቆት ? ከዚህ መሐል ችምቤዎች አንቺ ፣አንተ ፣ አንቱ እየተባሉ እየተሾሙ እየተሻሩ ፣ እየታሰሩ እየተፈቱ ተዝናንተው ይኖራሉ።

“ወደ አገር ቤት ጐራ ያልንማ እንደሆነ በእነ አፄ ቴወድሮስና በእነ አፄ ዮሐንስ ጊዜ ከጅብ አምልጦ የቀረ ቁርበት የመሰለ ጨርማዳ ጋሻ በብብቱ ያጠበቀና ባለቆዳ ወይም ሲሶ እንጨት ብረት መሳይ በጫንቃው አጋድሞ ዝቅ ያለ እንደሆነ ፣ አንድ እከካም ነፍጠኛ ብቻውን ያድር ከሆነ አንድ መንደር ሲያስር ሲፈታ ሲያስጨንቅ ነበር” ያሉት እውነት ከእውነትም በላይ ቢኖር ያንን ሆኖ እናገኛዋለን።

ፓሊስ እንደ ሽፍታ የሚፈራበት፣ የሚሸኝበት ፣ መንገድ ሲሄድ ስንቅ የሚሰነቅበት ፣ የሚያስገብርበት ቦታ መኖሩን የማያውቅ ቢኖር ምንኛ ደንቁሯል!! ከእርስዎ እጅግ የቀደመው ፕላቶ የተባለው ፈላስፋ ይኸንኑ ታዝቦ ወታደሮች እንዲህ ሊሆኑበት የቻሉበትን ምክንያት ሲያስረዳ ( ወታደር ሲሰለጥን እንደ ውሻ መሆን አለበት፤ የቤቱን ሰው የማይነካ የውጭውን ዘራፊና ሌባ የሚጠብቅ ፤ ጌታውን የሚያውቅ አገልጋይ መሆን አለበት። ቤተሰቡን የሚነክስ ውሻ ያበደ ነው። ሕዝቡን/ጌታውን /አሳዳሪውን የሚጋፋ ወታደርም ሥራውን አላወቀም ማለት ነው። ስለዚህ ትምህርት ጅምናስቲክ(ሰውነቱ እንዲጠነክር) ሙዚቃ (ልቡ እንዲለሰልስ) ያስፈልገዋል ብሏል።

የኛው ትምህርት ግን “ተከተል አለቃህን” ነው። ገደል ሲገባ ብታይ “ገደል ግባ” ነው። የሆነ ምሳሌ ቢያስፈልገን ያለፈው ዓመት ሰላማዊ ሰልፍ ለምን እንደተደረገ ተራ ወታደሩ ቀርቶ ሻለቆቹ እንኳን አለማወቃቸውን ሳያፍሩ አጫውተውናል።

**“ፓርላማውን ተቃውመን ነው ስንላቸው እኛ መንግሥት እንገልብጥ ያላችሁን መስሎን ነው እንጂ .....በማለት ተፀፅተው በለው! አልናቸው ! አሉ። በበለው ዓለም ውስጥ ነው ያለነው!!**

አፈወርቅ! ለርስዎ ጊዜ ብዙ የተለወጠ ይመስልዎታል። ለኔ በመጠን ይለያይ እንጂ በዓይነቱ የተለወጠ አይመስለኝም።

ስለ መጽሐፍዎ ጠቅላላ አስተያየት መስጠት ቢያስፈልግ በጊዜው የነበሩት ነጋድራስ ገብረሕይወት ባይከዳኝ ያሉትን ጠቅሶ ማለፍ ይበቃል።

“....ካቶ አፈወርቅ እጅ የታተመው ታሪክም ቢሆን ሙሉ አይደለም። ብዙውን ነገር በጨለማነቱ ይተዋል፣ ብዙ ነገር ያሳምራል ፣ በየዋሁና ጠንካራው የትግሬ ነገድ ይልቁንም እንደ ቦሬሳው ካሣ ያለ አርበኛ ከማንም ሰው እጅና አፍ ሊወጣ የማይገባው የስድብ ቃል ይገኝበታል። ዳግማዊ ምኒልክን ለማመስገን አፄ ዮሐንስ አራተኛን መስደብ የማያስፈልግ ይመስላል።”

በሉ አፈወርቅ ድርሻዬን ፈፅሜ እስከምከተልዎት ድረስ መሬት ይቅለልዎ እያልኩ እሰናበተዎታለሁ።

አክባሪዎ

ዋለልኝ መኰንን

/ ሥነ መ. III /

መጋቢት 18 ቀን 1960 ዓ.ም.